# ሙያ ሲጋለጥ!

(መልካም አዲስ ዓመት)

ውዷ ባለቤቴ- እመይቴ ስንዱ
አበደች ለየላት- አለሽ ሴቱ ወንዱ፤
ዛሬ በአዲስ ዓመት- ዛሬ በበዓሉ
ያቀረብሽው ድግስ- ምስክር ነው አሉ።

ባንድነት ማቅረብን- ቀላቅሎ ድግስን
ከትናንት ጀምሮ- ስናየው ሙያሽን
አበደች ነው ያልኩኝ- አወከሽ ጤናሽን።

ማ ይሙት! ባንድዬ! እንዲያው በየት አርጎ
በአንድነት ይቀርባል- ጠላ ተልባና እርጎ?
ምን አርገሽ ብትፈጭው- እንዴትስ ተቦክቶ
በርበሬ ከስንዴ-ጤፉ ከቡና ጋር -በአንድ ተዘጋጅቶ
ምን አይነት እንጀራ- ሊጋገር ነው ከቶ
ማን ፊት ነው እሚቀርበው- ይህ የአንች አነባብሮ?
እንጀራም አይመስል- በግዳጅ አንድ ሆኖ።

ትናንትም በአንድነት- ዛሬም በአንድ ጋግረሽ
ጤፍን በበርበሬ- መልክ ታሳጫለሽ
ሙያሽ ወፈፌ እንጅ- ጤነኛ አላሰኘሽ!

እባክሽ ተማሪ- ሙያ ከጎረቤት
ባለፈው ካየሽው- ከእነማሚቴ ቤት
ጤፉ እንጀራ ቢሆን- ለብቻው ተጋግሮ

በርበሬ ወጥ ቢሆን- ክሽን ብሎ አምሮ

ለብቻው በዓይነቱ- በመልኩ ተሰርቶ

ሙያ እንዲያ ነው እሚያምር- የሚታይ ውበቱ

አንድ ላይ በማብሰል- አያምርም ውጤቱ

አንድነት አንድነት- አትበይ በከንቱ።

ዳግማዊ ዳዊት
መስከረም 2003 ዓ.ም.
Ethio_dagmawi@yahoo.com